ጥር 24 ቀን 1998 ዓ.ም.

ይድረስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አባቶች፤
የተከበራችሁ አባቶች ቅዱሳን ጳጳሳት፣ መነኩሳት፣ አቡኖችና በልዩ ልዩ ደረጃ የቤተክርስቲያኒቱን ተግባር የምታከናውኑ ሃይማኖታዊ መሪዎች ሁሉ፤

ሰላም ለእናንተ ይሁን:: ሰሞኑን በከተራ፣ በጥምቀት እለትና በማግስቱም በቃና ዘገሊላ ክብረ በዓል እለት የተከሰተውን ረብሻና ውዝግብ በሚመለከት በየአድባራቱና ገዳማቱ ወይም በልዩ ልዩ  የሰበካ ጽ/ቤቶች ውስጥ ለሁለት ቀናት የዘለቀ ጉባኤ አካሂዳችሁ ውሳኔ ማሳለፋችሁን በቴሌቪዥን ከአዩና ከሰሙ ወገኖች አንዱ ነኝ:: የውሳኔያችሁ ይዘትም የዛሬ የጥር 24 ቀን 1998 እትም በሆነው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ  መጀመሪያ ገጽ እና 13ኛ ገጽ ላይ እንደሰፈረው «ማንነታቸው ያልታወቁ ግን ደግሞ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ቡድኖች ሃይማኖታዊ በዓላትን ከለላ አድርገው ፍላጎታቸውን ለማሳከት ሲሉ ታላቁን መንፈሳዊ የጥምቀት በዓል ማወካቸው ካህናትን፣ ምዕመናንንና የውጭ ሃገር ጎብኝዎችንም አሳዝኗል ሲሉ ገልጸዋል::» የሚል ነው:: በሃይማኖቱ ክብረ በዓላት ላይ ረብሻና ትርምስ ያስነሱት «ማንነታቸው ያልታወቁ ግን ደግሞ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ቡድኖች» የሚባሉት ለመሆኑ እንዴት ሳይታወቁ ታወቁ ተብሎ ቢጠየቅ ምን መልስ ይገኝ የሆን? ብቻ! ያም ሆነ ይህ በቴሌቪዥን የተላለፈውም ሆነ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የወጣው ዜና የሚያትተው ፍሬ ጉዳይ የአዲስ አበባ አድባራት፣ ገዳማት፣ ካህናትና የተለያዩ የሥራ ኃላፊዎች በስድስት የተለያዩ ቦታዎች ተሰብስበው የደረሱበት ድምዳሜ ከላይ የጠቀስኩትን ነው:: የዘገባው ሙሉ ይዘትም ይህንኑ ሀሳብ የሚያጎላና ድርጊቱ በአጠቃላይ ሲቃኝ የኢሃይማኖታዊነት መንፈስ የተጸናወተውና ከእግዚአብሄራዊ ተግባር ያልሆነ መሆኑን የሚያስረዳ መሆኑን ለመገንዘብ ችያለሁ::

ውድ አባቶች! እንዳላችሁት በሃይማኖታዊ በአላትም ሆነ መካናት አካባቢ ከአምልኮተ እግዚአብሄር፣ ከጸሎትና ምስጋና ውጪ የሆኑ ማናቸውም ኢሃይማኖታዊ ተግባራት መፈጸም የለባቸውም:: በዚህ ረገድ ፈጽሞ ትክክል ናችሁ:: ተፈጸሙ የተባሉት ተግባራት ግን እናንተ እንደጠቃቀሳችሁት ባልታወቁ ፖለቲከኞች የተፈጸሙ እንዳልሆኑ እናንተም እኛም እኩል የምናየው የኢትዮጵያ ቴሌቪዝን ያቀርብ በነበረው ዜና ዘገባና ሀተታ ሁሉ የተረጋገጠ የብዙዎች ጉዳይ ነበር:: ብዙዎች ያልኩዋቸውን ባለጉዳዮች ቀጥዬ ጠቅለል አድርጌ አቀርባለሁ::

በባለጉዳይነት የምጠቅሳቸው ሦስት ወገኖች ሲሆኑ፣ እነሱም፣ እናንተን የሃይማኖቱን መሪዎች፣ ጾጥታ እናስከብራለን ብለው የተሰለፉ ባለጠመንጃዎችንና ሰፊው አማንያንን ነው:: (የውጭ አገር ጎብኝዎችን ማዘን እንኩዋ ተውት!) እናንተ የሃይማኖቱ መሪዎች የምትመሩዋቸውን አማንያን በትክክል ስለመምራታችሁ፣ ስለማስተማራችሁ፣ ስለመገሰጻችሁና በምሳሌነት ስለመቆማችሁ፣ እግዚአብሄር የሰጣችሁን የእረኝነት ስልጣን በትክክል ስለመፈጸማችሁ አፋችሁን ሞልታችሁ፣ አንገታችሁን አቅንታችሁ፣ በዓይናችሁ ሙሉ እያያችሁ ትናገራላችሁ? እኛን የዋህ አማንያንን እመኑና ተከተሉ እያላችሁ እንደምትሰብኩን መጽሐፍ ቅዱሱን የምታምኑና የምትከተሉ ከሆነ በትንቢተ ሕዝቅኤል ም. ፴፬÷ ከቁጥር ፩ እስከ ፲ መጨረሻ የተዘረዘረውን በማሙዋላት ኃላፊነታችሁን ተወጥተናል ብላችሁ ቃላችሁን ትሰጣላችሁ? መጽሐፉ የሚለውን እነሆ:-

> .... እግዚአብሄር እንዲህ ይላል:- ራሳቸውን ለሚያሰማሩ ለእስራኤል እረኞች ወዮላቸው! እረኞች በጎችን ያሰማሩ ዘንድ አይገባቸውምን? ጮማውን ትበላላችሁ ጠጉሩንም ትለብሳላችሁ፣ የወፈሩትን ታርዳላችሁ፤ በጎቹን ግን አታሰማሩም:: የደከመውን አላጸናችሁትም፣ የታመመውንም አላከማችሁትም የተሰበረውንም አልጠገናችሁትም፣ የባዘነውንም አልመለሳችሁትም፣ የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም፣ በኃይልና በጭቆናም ገዛችኋቸው:: እረኛንም በማጣት ተበተኑ፣ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ፣ ተበተኑም:: በጎቼ በተራሮች ሁሉና በረዘሙ ኮረብቶች ሁሉ ላይ ተቅበዝብዘዋል፣ በጎቼም በምድር ፊት ሁሉ ላይ ተበትነዋል፣ የሚሻም የሚፈልግም አልነበረም::

ዛሬ ባለንበት ገሃዳዊ እውነታ ውስጥ በዚህ ጥቅስ ውስጥ የምናገኛቸውን እረኞች ሚና የሚጫወተው ማን ይመስላችሁዋል? በጎች የተባሉትስ? የእኔን የመጽሐፍ ቅድስ ጥቅስ እናንተም በየቁርባኑ፣ በየሐውልት ምረቃውና በየክርስትና ሥነ ሥርዓቱ ላይ የምትጠቅሱትና የምትሰብኩት በመሆኑ አዲስ ነገር ይሆንባችኋል የሚል ጥርጣሬ የለኝም፤ ለማስታወስ አመጣሁት እንጂ:: ለማንኛውም ልቀጥል::

ለመሆኑ ዛሬ እናንተ የምትተዳደሩበት ደሞዝ፣ የምትሰሩበት ጽ/ቤት ሁሉ ከየት የተገኘ ይመስላችሁዋል? ደመወዛችሁ የህዝብ ሀብት፣ ልብሳችሁም የህዝብ ሀብት፣ አጠቃላይ ዙሪያ ገባው የህዝብ መሆኑን ለአፍታም ትጠራጠሩ አይመስለኝም:: ታዲያ እነዚህ ህዝብ የሚባሉት አማንያን ሲደክሙ አጽናንታችሁዋል? ሲታመሙ አሳክማችሁዋል? ህመም መቼም አካላዊም መንፈሳዊም ነውና የናንተ ማሳከም የሚፈለገው በመንፈሳዊ ጠገጉ በኩል መሆኑን የሚያጣው የለም፤ ስለዚህ በመንፈስ የታመሙ ልጆቻችሁን ለማስታመም ምን ተግባር ተወጣችሁ?

በግንቦት 97 ምርጫ ወቅት የምርጫውን ሂደት ለመታዘብና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ታዛቢ ከመደቡት ተቋማት ውስጥ ቤተክርስቲያናችን ዋናዋ ነበረች:: በዚያም ሁላችንም ደስ ብሎን ነበር:: ምክንያቱም እውነትን፣ እምነትንና ትክክለኛ እግዚአብሄራዊ ፍርድን ለመናገር ከቤተክርስቲያን በላይ ማንም አይኖርም የሚል ጽኑእ እምነት አለና! ታዲያ የታዘባችሁትን ምርጫ ህዝባችሁ:- እንደትጠብቁት እንድታጽናኑት የተሰጣችሁ ህዝብ፣ ተጭበርብሬለሁ ብሎ ሲያምን፣ በየአደባባዩ ወጥቶ በአካል በአንደበቱ ሲጠራችሁ ተገኛችሁለት? ኤሎሄ! ኤሎሄ! ብሎ ሲጣራ ምን ነበር ምላሻችሁ? ለጥሪው መልስ ያጣ ህዝብ ምን እንዲሆን ትጠብቁ ነበር? ከእናንተ በላይ ታጋሽ፣ ጭምት፣ ትዕግስተኛ፣ የሆነውን እንዳልሆነ ተቀባይ፣ የታመመውን እንዳልታመመ አስመሳይ፣ የተጨቆነውን እንዳልተጨቆነ አድርጎ እሚቀበል፣ .... ህዝብ እንዲሆን ነበር ምኞትና ፍላጎታችሁ? ህዝብ እሚፈልገውን ሲያጣ፣ ድምጹን ሲሰረቅ፣ እምነቱን ሲካድ፣ መንፈሱ ሲናድ ወዴት ያመራ ይመስላችሁ ኖሮዋል? የመንፈስ ህመም፣ የህሊና መቁሰል አይገጥመውም ነበር ብላችሁ ታስቡ ነበር? ካሰባችሁ ተሳስታችሁዋል ብቻ አይበቃም፤ እግዜር የሰጣችሁንም የማመዛዘኛ ህሊና በወጉ ባለመጠቀማችሁ በእኔ እምነት ኃጢአትም ፈጽማችሁዋልና እሱ ፈጣሪ አምላክ ይቅር ይበላችሁ! እላለሁ::

ህዝብ በእምነት ቤት ውስጥ ሰብስቦ ከያዘው አዳራሽ ውስጥ የሚፈልገውን ሲያጣ፣ ጨኸቱን የሚሰማለት ሲያጣ፣ ተስፋ ይቆርጣል፤ መሄጃ ያጣል:፤ መላ ቅጡ ይጠፋዋል:: በዚህ ጊዜ ይበተናል፤ ይቅበዘበዛል፤ ለአራዊትም ይዳረጋል:: በዚህን ጊዜ የራሱን ከችግር የመውጫ መንገድ ይቀይሳል:: ክህመሙ ለመዳን፣ ከስብራቱ ለመጠገን፣ ከመበተንና በአራዊት ከመበላት ለመዳን ሲል የሚቀይሰው መንገድ እንዳይበላሽ አስቀድማችሁ ማበጀት የሚገባችሁ እናንተ ነበራችሁ:: ይህን እንዳላደረጋችሁ ታውቁታላችሁ::

ለመሆኑ ህዝብ የታመመበትን የምርጫ ጉዳይ፣ መንፈሱ የተሰበረበትን የምርጫ ጉዳይ፣ እምነቱንና ድምጹን የተነጠቀበትን የምርጫ ጉዳይ እናንተ ምን አላችሁለት? ምን አላችሁበት? በዚህ ሰበብ አደባባይ ወጥቶ ሲጮህ ምን የማጽናኛና የማረጋጊያ ተግባር ፈጸማችሁ? ከህመሙ እንዲፈወስ፣ ከቁስሉ እንዲድን፣ ከእምነቱ እንዲገኝ፣ ምን አላችሁለት?

ሰኔ 1 ቀን 1998 ዓ.ም. ያ ሁሉ ህዝብ ወጥቶ በተኩስና በቆመጥ ሲለሸለሽ እናንተ ምን አላችሁ? የእናት አባቶቻችን ድምጽ ይከበር ብለው በጮኹ ተማሪዎች ላይ፣ ድንጋይ በሚወረውሩ ህጻናትና ወጣቶች ላይ፣ የጥይት ሩምታ የሚያርከፈክፉ ገዳዮችን ምን ተናገራችሁዋቸው? በየትኛውስ ወገን ቢሆን ሰው ሰው አይደለም ወይ? በአመጸኛነት የተፈረጁተም ሆኑ የፈረጁዋቸው ሁሉስ ቢሆኑ ሰዎች አይደሉም? የእግዚአብሔር ፍጡራን አይደሉም? ሰው እንዳይሞት፣ ነፍስ እንዳይጠፋ፣ አካል እንዳይጎድል እናንተ ምን ምልጃ፣ ምን ምክር፣ ምን ተግሣጽ ሰጣችሁ- አደረጋችሁ?

ይኸ ሁሉ ተጠረቃቅሞ መስከረም እስኪጠባ፣ መስቀል እስኪደርስ የት ነበራችሁ? እናንተን ከፈጣሪው ቀጥሎ ለሚያምን ህዝብ፣ ከጉርሱና ከልብሱ ቀንጥቦ ለሚያኖራችሁ ህዝብ፣ እንዲያው ለራሱ ሳይሆን አንዳንዴ ለእምነቱና ለቤተ እምነቱ ሲል ስቃይ- መከራ

ለመቀበል የተፈጠረ ለሚመስለው ህዝባችሁ አብረዋችሁ ምርጫ የታዘቡ የውጭ አገር ዜጎች ሳይቀሩ ለኢትዮጵያ ህዝብ ሲመሰክሩ፣ በደሉን በአደባባይ ሲያወግዙ እናንተ ምን? መቼ? ድምጻችሁ እንኳዋ ተሰማ! ከካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በስተቀር ለመሆኑ የትኞቹ የእምነት ቤቶች ለህዝብ ቆማችሁ? ለህጻናት፣ ለሴቶች፣ ለአእሩጋን፣ ለወጣትና አዛውንቶች ስቃይና መከራ ድምጽ አሰማችሁ? ገዳይ እያለ ሙዋችን ስታወግዙ፣ ተቀባይ እናገኛለን፣ ሰሚ እናገኛለን ብላችሁ ነው? ወይስ ጭርሱኑ እንደፈለጋችሁ እያሰባችሁ የምታርዱን፣ እየገፈፋችሁ የምትለብሱን በጥሬ ትርጉሙ በጎች መሰልናችሁ?

እሺ ይኸም ይቅር ጥቅምት 22 ቀን 1998 ጀምሮ እስካሁን ድረስ አጠቃላይ ከተማው፣ አጠቃላይ አገሩ ሽብር ሲነግሥበት እንዴት «አንተም ተው! አንተም ተው!» ማለት ተሳናችሁ? ወይስ አልነበራችሁም? ከሰኔ 97 እስከ ህዳርና ታህሳስ 1998 ድረስ ምን ስትሠሩ ከረማችሁና ነው አሁን ተነስታችሁ «ማንነታቸው ያልታወቁ ግን ደግሞ የፖለቲካ ዓላማ ባላቸው» በማለት ራሱ ከፖለቲካ ያልጸዳ ኢሃይማኖታዊነቱ የሚጎላ ውግዘት ለማዥጎድጎድ የበቃችሁት? ከታህሳስ 26 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ በየህጻናት መዋያው፣ በየአንደኛ ደረጃና በየሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቱ የሚገኙ ደቂቀ አዳም ወሄዋን ሁሉ ተሰብስበው ዋይ! ሲሉ ኡኡ! ሲሉ እናንተ ምን አላችሁ? ምን ደወል አቃጨላችሁ? ምን መለከት ነፋችሁ? ከነፃነትና ከባርነት፣ ከእምነትና ከክህደት፣ ከክብርና ከውርደት የቱ ይበልጥ ይመስላችሁና ነው የታወቀ ችግር በታወቁ ሰዎች ላይ ያስከተለውን መዘዝ ለመሸፋፈን «ማናነታቸው ያልታወቁ» በማለት መግለጫ የምትሰጡት? ኧረ! በታላቁ ፈጣሪ በእግዚአብሔር ብላችሁ ጨርሶ እምነታችንን አትፈታተኑት::

ለእናንተ ይመስላችሁ ይሆናል እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ የሃይማኖቱንና የሃይማኖት መሪዎቹን ለይቶና አበጥሮ የሚያውቅ ነው:: ይህ በታሪክም የተረጋገጠ ነው:: የደብረሊባኖስ ገዳምን አባቶች የጣሊያን ፋሽስት እንዳሉ በጥይት ሲቆላቸው፣ በእሳት ሲያንጨረጭራቸው፣ አቡነ አብርሃም በጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩ፣ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ለመምራት በጣሊያን የተሰጣቸውን ሹመት ተቀብለው ነበር፤ በአንጻራቸው ግን አቡነ ጴጥሮስ ለኢትዮጵያ ህዝብ ለእምነትና ለነጻነት መሞት ቅዱስ ሞት መሆኑን አብስረው፣ መስቀላቸውን በደረታቸው ላይ አንግተው፣ እመነትና ጽናትን በኢትዮጵያ ምድር ላይ ተክለውና ዘርተው በአደባባይ በመትረየስ ተደበደቡ!! ነፍሳቸውን እግዚአብሔር ከጻድቃንና ከሰማእታት ጋር ያኑርልን! አሜን!

ዛሬ እንደእናንተ ዓይነቶቹ በጊዜያዊ ጥቅምና በፖለቲካ ነፋስ በተወሰዱ የሃይማኖት መሪዎች ነን ባዮች ጋር የተቧደኑ አባሪ ተባባሪዎች መኖራቸው ሀቅ ቢሆንም በየገዳማቱ፣ በየአድባራቱ፣ በዱር በገደሉ ሁሉ ለተበደሉ የሚጮሁ፣ የሚታሰሩ፣ የሚገረፉ፣ የሚሳደዱ፣ የሚገደሉ፣ ስሙር አባቶች እንዳሉንና እልፍ አእላፋትም እንደሆኑ እናምናለን:: ይብላኝ ለእናንተ እንጂ!

የተከበራችሁ አባቶች፣ ይኸን ሁሉ ስላችሁ በጭፍን መንግሥትን የተቃወሙትን ሁሉ ደግፉ፣ እሱን ደግሞ አውግዙ እንዳላልኩ እወቁልኝ:: እኔ ጥፋተኛን ማውገዝ የተገባ መሆኑን ሳምን የጥፋትን መሰረት እረስቼ አይደለምና እሱን- የጥፋትን መነሻን- እንድትመለከቱ ያልሞከራችሁብትን ድርጊታችሁን መውቀሴ ነው::

ባለፈው ጥምቀትና ቃና ዘገሊላ ላይ ተከሰተ የተባለው ችግርና ትርምስ ምንጩ ምንና የት ይመስላችሁዋል? እርግጥ በቴሌቪዥን በተላለፈው መግለጫችሁ ላይ እንደሰማነውና በጋዜጣው ላይ እንዳነበብነው ማንነታቸው ያልታወቁ ግን ደግሞ የፖለቲካ ዓላማ ያላቸው ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ያደረሱት ረብሻ ይመስላችሁዋል? እውነት! ሁላችሁም የእምነቱ አባቶችና ተሰብሳቢዎች እውነት! የተላለፈውን መግለጫ ታምኑበታላችሁ? እውነታችሁን ከሆነ፣ የምታምኑበት ከሆነ፣ አገራችን ሌላ አደጋ ገና ይጠብቃታልና «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» የሚለው የቅዱስ ዳዊት ቃል አሁን ነው ጎልቶ መነገር ያለበትና አጥብቃም እንድትዘረጋ መማጸን የሚያስፈልገን::

ስንትና ስንት ዘመናት በሰላምና በጽጥታ፣ በእርምሞና በእርጋታ፣ በእስክስታና በሆታ፣ በፈንጠዝያና በደስታ ወጥቶ፣ ተከብሮና ታጅቦ የሚመለስ ታቦት በዘንድሮው ልማዳዊ ሥነ ሥርዓቱ ላይ ምን ተፈጠረና ነው በእልፍ የሚቆጠሩ ዥጉርጉር

አረንጉዋዴ ለባሾች፣ ጠመንጃ አንጋቾች፣ ሽመል ሰባቂዎች፣ የካራቴና ውሹ ኩነጉፉ ሰልጣኝ ፓራ ኮማንዶዎች በአጃቢነት የተሰለፉት? ስንትና ስንት አይነት ጥበባዊ ፈጠራዎች ይቀነቀኑበት የነበረውንስ ጥምቀተ ባህር ወና እስኪመስል ጭር ማሰኘት ምን አመጣው? የህዝብን ዘላቂ ማህበራዊ ትስስር ማስከበሪያ የሆነውን ቦታ ለመቆጣጠር ምን አነሳሳቸው? እናንተስ ጎምቱ ጎምቱ የሃይማኖቱ አባቶች ምን አሰኝቶአችሁና ምን አስግቶአችሁ ነው በዚያን አይነት ቅጥ ባጣ ጥበቃ ውስጥ የወደቃችሁት? የጥንት አባቶቻችን ያገር ድንበር ሲያስከብሩ ታቦታትን ጦር ሜዳ ድረስ ይዘው ይሄዱ ነበር መባሉን ሰምተናል፤ አንብበናልም:: ታዲያ እነዚን ታቦታት ይዘዋቸው ይሄዱ የነበረው በቀሳውስቱና በካህናቱ ሽክምና እቅፍ እንጂ እንደሌላው ስንቅ ሁሉ በአጋሰስ ጭነው እንዳልነበር የሚታመን ጉዳይ ነው:: ታዲያ ዳር ድንበር ለማስከበር እግራቸውን ለጠጠር ግንባራቸውን ለአረር ይሰጡ የነበሩ ቀሳውስትና ካህናት ይመሩዋት በነበረች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአሁኑ ጊዜ፣ ምን ተፈጠረና ነው የወታደር አጃቢ፣ ያውም አነጣጣሪ ተኩዋሽ ያስፈለገው?

ለእኔ እንደሚመስለኝና እንደማምንበትም ችግር መኖሩን አስቀድማችሁ ታውቃላችሁ ማለት ነው:: አስቀድማችሁ ካወቃችሁ ደግሞ ምን ሠራችሁ? ለምንስ እምታውቁትን እውነተኛ ችግር ችላ አላችሁት? ለምን በእግዚአብሄር የተሰጣችሁን የእረኝነት ስልጣን ዘነጋችሁት? ጠብቁት፤ አስታምሙት፤ ሰብስቡት፤ አድኑት፤ ተንከባከቡት ተብሎ የተሰጣችሁን ህዝብ « ህዝቤን ወዴት አደረሳችሁት?» ብትባሉ መልሳችሁ ምን ይሆናል? ለምን የችግሩን ሥረ መሠረት እየረመረማችሁ ጫፍ ቅርንጫፉን ትቸፈችፋላችሁ? በሁሉም ወገን ውስጥ የሚብላላውን እውነተኛ ችግር ለማስወገድ ከናንተ ከሃይማኖቱ አባቶች ሌላ ምንን እንዲፈልግላችሁ ነው ህዝቡን የምታወናብዱት?

በጃን ሜዳ፣ በየካ ሚካኤል፣ በጭቁኑ ሚካኤል፣ በአዲሱ ሚካኤል፣ ያ ሁሉ ትርምስና ሽብር፣ የእናንተንስ አባትነትና እግዚአብሔርን አማኝነት የሚያስጠረጥር ተግባር የተፈጠረው እርግጥ ማንነታቸው ባልታወቁ ፖለቲከኞችና ቡድኖች ይመስላችሁዋል? እንዳትሳሳቱ!! ፈጽሞ የሚታመን አይሆንም የናንተ መደምደሚያ! ይልቁንስ እምነቱን በተሰረቀ፣ የመንፈስ ስብራትና ህመም በአጋጠመው፣ ሰብሳቢና መካሪ ባጣ- በነጣ- በገረጣ እንዲሁም የተስፋው ደብዛ በጠፋበት የእግዚአብሄር «በግ» ሁሉ ልቦና ውስጥ የተፈጠረ ችግር ነው ማለትና ለመፍትሄው መነሳሳት ነበር የሚገባ!!

ቀደምት አባቶች እንኩዋን እንዲህ ያለ ሰፊ አገራዊ ትርምስና ሽብር ተከስቶ ይቅርና በሁለት ባላንጣ ግለሰቦች መካከል አደገኛ የሚመስል ችግር ሲፈጠር መስቀል አውጥተው፣ ታቦት ተሸክመው በዳይንም ተበዳይንም ለምነው፣ መክረውና ገሥጸው ዕርቀ ሰላም ያወረዱ ነበር እንጂ «የማይታወቁ ግን የፖለቲካ ዓላማ የሚያራምዱ» በማለት የወንጃይነትም ሆነ ያሰወንጃይነት ሚና ኖሮአቸው አይቼም ሰምቼም አላውቅም:: እናንተስ ብትሆኑ ባሳለፍናቸው አስርና አሥራ አምስት ዓመታት ውስጥ ስንትና ስንት ጊዜ ነው ልብሰ ተክህኖ ለብሳችሁ፤ መጎናጸፊያ ደርባችሁ ፣ መስቀላችሁን አስቀድማችሁ መንግስት በጠራው የድጋፍ ሰልፍ ላይ የወጣችሁት? አሁን አጠቃላይ ቀወስ ለመፍታት ይህንን ማድረግ ምን፣ ማን ከለከላችሁ? የሃይማኖት አባቶች የሃይማኖት አባትነት ዋናው ማረጋገጫ በህዝብና በህዝብ፣ በህዝብና በመንግሥት በአጠቃላይ በአገር ውስጥ ሰላምና መረጋጋት ይኖር ዘንድ ማበረታታት ይመስለኛል:: በመግለጫው ላይ እንደተጠቀሰው የማይታወቁ ሰዎች እንኩዋ ቢኖሩ ለማወቅና ችግሩን በእግዚአብሄራዊ መንገድ በሰላማዊና በምክክር ዘዴ የሚወገድበትን ሥልት መቀየስና ማበጃጀት እንጂ «እንዲህ ዓይነቱ ድፍረት ዳግመኛ እንዳይደገም ....» ዓይነት ማስፈራሪያ እንኩዋን ለሚስፈራራው ለአስፈራሪውም አይጠቅም!!

አባቶች ጳጳሳት፣ ካህናትና ልዩ ልዩ የቤተክህነቱዋ አስተዳዳሪዎች እባካችሁን ለሚያያልፈው ዓለማዊ መንግሥት ብላችሁ ዘላቂውንና ዘለዓለማዊውን የእግዚአብሄር መንግሥት አትበድሉ:: ካህናቱ ያወጣችሁት መግለጫ «እንዲህ ዓይነቱ ድፍረት ዳግም እንዳይከሰት አጥፊዎች ከተግባራቸው እንዲቆጠቡ ....» ማሳሰባችሁን ያትታል:: እንዲህ ዓይነቱ መግለጫ ፖለቲካዊ እንጂ ከቶውንም ሃይማኖታዊ ሊባል አይበቃም:: ያላችሁትን እንቀበልና፣ ለመሆኑ እንዴት ነው ልትቆጣጠሩት የምትችሉት? ምን ልታደርጉ?

ረባሽን «ረባሽ»፣ አጥፊን «አጥፊ»፣ ገዳይን «ገዳይ» ለማለት የሚያስችል ሰማዕትነትን የሚጠይቅ ርምጃ የመውሰድ ብቃትና ዝግጅት ከነመንፈሳዊ ክብሩ አላችሁ? አልሚውን «አልሚ»፣ ሥልጡኑን «ሠልጡን» የማለትስ ጽዱ መንፈሳዊ ልእልና ይኖራችሁ ዘንድ ለእኛ ለ«በጎቻችሁ» ያሳያችሁበት አጋጣሚ ትዝ ይላችሁ ይሆን? እመግለጫው ውስጥ የጠቆማችሁዋቸው «ሕዝቡን የሚያሳስቱና ቤተክርስቲያኗ የማታውቃቸው በየአደባባዩ የሚያስተምሩ ሐሰተኞች» የተባሉት እውነት ሐሰተኞች ቢሆኑ ህዝብን የማሳሳት ብቃት ይኖራቸዋል ብላችሁ ጥቅል ውሳኔ ስትሰጡ ትንሽ እንኳ ለህዝብ ክብር አለመስጠታችሁ ከማስተዛዘብ ያለፈ ፋይዳ ያለው ይመስላችሁዋል? እኔ አይደለም! አይሆንም ብዬ አምናለሁ:: ህዝብ ለሰባኪ ሁሉ ጆሮውን ሰጥቶ የሚያዳምጠው ጥሬውን ከብስል፣ ፍሬውን ከገለባ፣ ሐሰቱን ከዕውነት የመለየት ብቃትና ችሎታ ስላለው ጭምር መሆኑንም ትንሽ ግምት ብትሰጡት ትጠቀሙበት እንደሆነ እንጂ አትጎዱበትም ብዬ አስባለሁ:: ለማንኛውም በየትኛውም አጋጣሚና እለታዊ ሁኔታ ውስጥ ሰው እንዳይሰበሰብ ልታሳውጁ ካልሆነ በስተቀር ምን በማድረግ «ድፍረቱን» እንደምታስወግዱ ሲደርስ እምናየው ይሆናል:: አደራ! ለቀብር መጠራራትን እንዳትከለክሉን ብቻ!

በማናቸውም ሁኔታ የሚሰሙ የህዝብ ሮሮዎችን፣ አቤቱታዎችን፣ ለቅሶና ዋይታዎችን አለባለቤታቸው ባለቤት እየፈለጉ መዳለሉ፣ አለምህኛቱ ምህኛት እየፈለፈሉ መዝራት ለማንም አይበጅም፤ በተለይም ሰፊ የህሊና እምነተኛ ለሆነ ወገን አይሆንም፤ ይበልጡንም ደግሞ በኃላፊነት ቦታ ተገኝተው ህገ እግዚአብሄርን እናስፈጽማለን ለሚሉና ሃይማኖታዊ ውክልና ለተቀበሉ አባቶች አጥፊያቸው ይመስለኛል::

ለሰው ልጅ መብት፣ እምነትና ነፃነት ቀናኢ ሆኖ መታገል፣ መሥራትና መጮህ በአምላክ ዘንድም የሚያስወቅስ አይደለምና ከሃይማኖት አባቶቻችን የምንጠብቀው ምክርና ትምህርት ከዚሁ አንጻር የተቃኘ፣ ጥፋትን ብቻ ሳይሆን የጥፋትን ምንጭ በማድረቅ ረገድ አስተዋጽኦ የሚኖረው ተግሣጽ፣ በተስፋ ላይ ከሚሰነዘር ዛቻና ማስፈራራት ይበልጥ እምነት፣ ተስፋና ቀና መንፈስ በህዝብ ህሊና እንዲሰርጹ፣ በአንደበቱም የሚነገሩ እንዲሆኑ የሚያመቻችና የሚያስችል መግለጫ ነው::

ውድ አባቶች ጳጳሳት፣ መነኩሳትና ካህናት እያንዳንዳችሁ ለቆማችሁለት ህገ እግዚአብሄር ብላችሁ፣ እንድትጠብቁት አደራ ለተሰጣችሁ ህዝብ ብላችሁ፣ ለአገር፣ ለታሪካና ለትውልድም ዘላቂ ደህንነት ብላችሁ፣ የሚያስማማ መንፈሳዊ አርማችንን አክብራችሁ አስከብሩልን፤ ይህም ካልሆነላችሁ ለግል ነፍሳችሁና ንብረታችሁ አስባችሁ፣ ሰዋዊ የሆነውን ይሉኝታንና የነገን ትዝብት ፈርታችሁ አገሪቱ እንድትረጋገና ሰዎች በአካልም በህሊናም እንዳይጨቆኑ ምከሩ፤ የተጨቆኑት፣ የታሰሩትና የተሰደዱት ነፃነታቸውን ይጎነጸፉ ዘንድ ተጣጣሩ እንጂ! «ወንድሞች ሆይ፣ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ፣ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤» ኤፌ. ፮፥ ፩:: የተባለውን ትሆኑልን ዘንድ እንሻለን እንጂ እመጀመሪያው ጥቅስ ላይ እንደተገለጸው «በኃይልና በጭቆና ገዛችኋቸው::» እንደተባሉት እረኞች አትሁኑብን:: «ወዮላቸው» ማለቱን አትዘንጉ! እግዜር ጥሎ አይጥለንምና::

ለአገራችን ሰላም ያውርድልን!
ለበደሉ የንስሀ መንፈስን፣ ለተበደሉ የይቅርታንና የመጽናናትን ልቦና ችሩ እግዚአብሔር ይላክልን!

አሜን!

አክባሪና ታዛዥ ልጃችሁ
አሰፋ ኃይሌ ማሞ